የረቡዕ ሚያዚያ 19 1997ዓም ( ኤፕሪል 27 2005)

## የፍኖተ ዴሞክራሲ ሐተታ

## ጦርነትን እንደ መያዣ

ረሀብ ይከላል ባቄላ፥ ከብርድ ያድናል ነጠላ እየተባለ፥ በጥንታዊቷ ኢትዮጵያ ሲነገር ነበር ብለው የሚያወጉ አዛውንት እንደነበሩ ትዝ ይለናል። የዚህን የጥንታዊ አባባል ትርጉም በትክክል ለማወቅ ባይቻልም፥ ምናልባት ሁሉም ለችግር ጊዜ፥ ይረዳሉ የሚል መልዕክት ይኖራቸዋል ተብሎ ይገመታል። ሠላም ለማግኘት ከፈለክ፥ ለጦርነት ዝግጁ ሁን የሚባል መመሪያ ያላቸው ሀገሮች በርካታ እንደሆኑ የሚሳት አይደለም። አብዛኛው የዓለም ሀገሮች ጦርነትን የሚፈልጉ ባይሆንም፥ ጦርነትን እንደ ብሔራዊ ፖሊሲያቸው የወሰዱ ጥቂት ሠላም ነሽ መሪዎች ስላሉ፥ ከእነርሱ ጦርነት ለመከላከል፥ በግድ ለጦርነት ተዘጋጅቶ መጠበቅ አስፈላጊ ይሆናል። የጦርነት መንስዔው፥ ሂደቱና ውጤቱ ምን እንደሆነ በዓለም ታሪክ ሰፊውን ቦታ የያዘ ስንክሳር በመሆኑ፥ ያንን ለመዳሰስ አንቃጣም። ያ እንዳለ ሆኖ ግን፥ በዘመናችን የተፈጠሩ ጥቂት ድኩማን መሪዎች፥ ለራሳቸው ጥቅምና ርዕዮተ-ዓለም ብቻ ሲሉ፥ ጦርነትን እንደ ብሔራዊ ፖሊሲያቸው በመውሰድ፥ አስፈላጊ ሆኖ በሚታያቸው ጊዜ ሁሉ ጦርነት ያነሳሉ። ብዙ ሕይወት ያጠፋሉ። ጎልቆ- መሳፍርት የሌለው ኃብት- ንብረት ያወድማሉ። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎችን ከኑሯቸው ያፈናቅላሉ።

እነኝህ የጦርነት አባዜ የተጠናወታቸው የሀገር መሪዎች፥ ልባቸው ቀዝቃዛ፥ ጭንቅላታቸው የፈላ በመሆኑ፥ ለሰው ልጅ ዕልቂትና ጥፋት፥ ርኅራኄ ቀርቶ፥ ዝቅተኛ ድንታ እንኳን አይሰማቸውም። በሌላው ሀገር ያሉትን መሪዎች እንተውና፥ ለዚህ አባባል ተስማሚ ምሳሌዎች የሚሆኑትን፥ የኛዎቹን ድኩማን፥ መንግሥቱ ኃይለማርያምና መለስ ዜናዊን ለመጥቀስ እንገደዳለን። ያገዛዝ ዘመናቸውን በጦርነትና በሽብር ጨርሰው፤ ሀገር አጥፍተው፥ ሕዝብ አስጨርሰው እነርሱም ይጠፋሉ። ሀገሪቱም እንደገና ከትቢያ ለመነሳት ትፍጨረጨራለች። አንገቷን ቀና ለማድረግ በምትጣጣርበት ወቅት፥ እንደገና ወደሌላ ጦርነት የሚዘፍቋት መሪዎች ይነሳሉ። በዚህ የጦርነት አባዜና አዙሪት በመግባት ዜጎቿ በማያቋርጥ የእሳት ነበልባል ይገረፋሉ። የዘለዓለማዊ ሰቆቃ ሰለባ ይሆናሉ።

የኢትዮጵያ አምባገነን መሪዎች፥ ጦርነትን እንደ መንግሥታዊ መመሪያቸው አድርገው የሚይዙት፥ እንደ ሌሎቹ ሀገሮች ( መሪዎች) አምባገነኖች፥ የሀገራችውን ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ፥ ሀገር ለማስፋፋት፥ ወይም የተወሰደ መሬት ለማስመለስ፥ ወይም ደግሞ የሀገራቸውን ስትራተጂያዊ ደኅንነት ለማስከበር፥ ብሎም፥ ከጥቃት ለመከላከል ሳይሆን፥ በአመዛኙ፥ የአገዛዝ ዘመናቸውን ለማራዘም፥ጊዜያዊም ቢሆን የሥልጣን መደላድላቸውን ለማረጋጋት፥ ተቃዋሚዎቻቸውን ለመደምሰስና ሕዝቡን

እያሸበሩ ለመግዛት ብቻ ለመሆኑ÷ የሚካድ አይደለም። የአንድ ሀገር የውስጥ ፖሊሲ÷ የውጭ ፖሊሲው ትክክለኛ ነፀብራቅ እንደመሆኑ÷ የኢትዮጵያ አምባገነን መሪዎች የጭቆና አገዛዛቸውም÷ ለሁለንተናዊው ጉዳይ ቀጥተኛ አስተጋብዖ ይኖረዋል። የኢትዮጵያ አምባገነን መሪዎች የተበላሸ የውስጥ ፖሊሲ÷የውጭ ፖሊሲያቸውንም አበላሽቷታል። መላ-ቅጡን አሳጥቶታል። አገዛዛቸው የተመሠረተው፤ በሽብር፤ በፍርኃት-በማስፈራራት፤ ሕዝብን በመበደልና በጭቆና ስለሆነ÷ የውስጥ ሠላምን አያስገኝም። ገዥዎቹም ሠላምን ሊያገኙ አይችሉም። ይህንን የተበላሸ የውስጥ ፖሊሲያቸውን የሚደግፉላቸው የውጭ ኃይሎች ብቻ ስለሆኑም÷ ለዓላማቸው ማሳኪያ የሚሆን የጦር መሳሪያ በገፍ ያቀርቡላቸዋል። ይህ ክስተት ደግሞ÷ ሁለት ተፃራሪ ኃይሎች በሁለት ጎራ ተከፍለው በኢትዮጵያ የፖሊቲካ ምልከዓ-ምድር ተፋጥጥው እንዲከሰቱ አድርጓቸዋል። በአንድ በኩል የኢትዮጵያ አምባገነን ገዥዎችና የውጭ የበላይ ጠባቂዎቻቸው ሲሆኑ÷ በሌላው በኩል ደግሞ÷ ተጨቋኙ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። ሁለቱም ክፍሎች ተፃራሪ ጥቅሞች ስላሏቸው ሊታረቁም ሊስማሙም አይችሉም።

ይህ ነባራዊ ሁኔታ ደግሞ÷ ለኢትዮጵያ አምባገነን መሪዎች አንድ ዘለዓለማዊ የሆነ ፖሊሲ እንዲነድፉ ምክንያት ሆኗቸዋል። ይኸውም÷ ጦርነትን እንደ መያዣ እየተጠቀሙ ሕዝቡን በማያቋርጥ ፍርኃትና ጭንቀት ውስጥ አስገብተው ሊያስፈራሩት አስችሏቸዋል። ሕዝብ ሲጨቆን÷ ከጭቆናው ለመላቀቅ ጥረት ማድረጉ ስለማይቀር÷ ይህ ከመሆኑ በፊት ገዥዎቹ አቅጣጫውን የሚያስተው÷ ትኩረቱን የሚያዘናጋውና ኃይሉን የሚበታትነውን ዘዴ ያዘጋጃሉ። ለዚህ ዘዴያቸው፤ እስካሁን ፍቱን መዳኀኒት ሆኖ ያገኙት÷ ጦርነትን እንደመያዣ እየተጠቀሙ ሕዝቡን ለዚህ ፕሮፓጋንዳ ሰለባ ማድረጋቸው ነው። ይህንን ዘዴ በመጠቀም እስካሁን የወያኔ መሪዎች የሚስተካከላቸው የሌለ ይመስላል። የሀገሪቱ ሁለንተናዊ ችግሮች እየተባባሱ መሄዳቸው÷ ጭቆናው እየተደራራበ መምጣቱ ብሎም ሕዝቡ ለአመፅ መዘጋጀቱ÷ በሀገሪቱ ክፍሎች የአልገዛም ባይነት መበራከቱ÷ ሕዝቡ የሚጠብቀውን ያህል ባይሆንም እንኳ÷ የተቃዋሚው ኃይል በአንድ ዓላማ ዙሪያ በመሰባሰብ ላይ መሆኑ÷ የዓለም አቀፍ ሁኔታ እየተለወጠ መሄዱና የመለስ ዜናዊ የበላይ ጠባቂዎችም ቀስ በቅስ ፊታቸውን እያዞሩበት መሆናቸው÷ የዚህን ዘረኛ ሥርዓት ዕድሜ ለማሳጠር የማስጠንቀቂያ ደወል የሚያሰሙ ሆነዋል። የዚህ ሁሉ ድምር ውጤት ታዲያ÷ መለስ ዜናዊና ግብረ አበሮቹ የሚይዙት የሚጨብጡት ማጣት ሆኗል። ከዚህ መርበትበትና ድንጋጤ ለጊዜያዊም ቢሆን መተንፈሻ ማግኘትን ይፈልጋሉ። ይህንን መተንፈሻ ለማግኘት ደግሞ፤ ለዚህ ወቅት ይጠቅመናል ብለው ያቆዩትን የፖሊቲካ የቁማር ካርታ መምዘዝ ይሆናል። እርሱም ጦርነትን÷ እንደ መያዣ÷ እንደ ማስፈራሪያ÷ እንደ ሽብር መልቀቂያ÷ እንደ አስቾኳይ የክተትና የሽብር አዋጅ ማደናገሪያ መጠቀም ይሆናል። ለዚህ የማስፈራሪያ ማጠየቂያ የሚጠቀሙበት ደግሞ÷ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለሀገሩ ሟችነቱን÷ ለነፃነቱና ለሀገራዊ ልዕልናው ቀናዒነቱን ነው። ያው ጊዜ ያለፈበትን÷ ያረጀ ያፈጀ የተረት ተረት ፕሮፓጋንዳ ወቅታዊ ቀለም ቀብቶ ቡታ መስደድ ነው። እነርሱ

ራሳቸው ሀገር እንዳላስቆረሱ፥ ሕዝብ እንዳልከፋፈሉ፥ ድንበር እንዳላስደፈሩ፥ የሀገሪቱንም ግዛታዊ ልዕልና እንዳላዋረዱ ሁሉ፥ ዛሬ እነርሱ እንደገና ተገልብጠው፥ ሀገርህ ተቆረሰች፥ ተወረረች፥ ድንበርህ ተጣሰ፥ ግዛታዊ አንድነትህ ተናጋ፥ በማለት ሊያውጁ ይዘጋጃሉ። የሕዝብን አመፅ አቅጣጫ ለማስቀየር፥ ሽብር ተፈጥሮ በሚከተለው ግርግር የተቃዋሚ ድርጅቶችን ለማጥፋት፥ ሕዝባዊ አመፅን ለማፈን፥ ፀረ ወያኔ እንቅስቃሴን ለማዳፈን፥ የዓለም አቀፍን ዕይታ ለመበረዝ፥ እነመለስ ዜናዊ የማይበጥሱት ቅጠል አይኖራቸውም። ለዚህ መርትበታቸው ይጠቅመናል ብለው ያቆዩት የከተት አዋጅ፥ የጦርነት ከበሮ፣ የሽብር ቀረርቶ፥ ካለኛ በቀር ሀገር ወዳድና ግንባር ቀደም ሚች ላሳር ነው የሚል አስቂኝ ምፀት ነው። ይህን ድራማ ቢሰሩ አይፈረድባቸውም። ምክንያቱም፥ የሕዝቡን የማሰብ ችሎታና የአዕምሮ ብስለት በደንብ አውቀነዋል ብለው፣ ራሳቸውን አታልለው፥ ይህንንም አምነው በመቀመጣቸው ነው። ያለፈውን ስናይ ደግሞ ጥረታቸው ሙሉ በሙሉ ውጤት አልባ ነበረ ለማለት አንደፍርም።

አያሌ የፖለቲካ ጠበብቶችም ሆኑ የኢትዮጵያን ሕዝብ ታሪክና ባኅል፥ ባኅርይና መስተጋብር እናውቃለን የሚሉ የታሪክ ተመራማሪዎች ለማለት የሚሹት አንድ ነገር አለ። ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ እስከዛሬ ድረስ ማንነቱን በሚገባ የሚያውቅለት መሪ አግኝቶ አያውቅም ይላሉ። ብዙ ታዛቢዎች ይህን አባባል ከዕውነት የራቀ ነው ማለት አይቻልም ሲሉ ይሰማሉ። በዚህ አባባል ሁሉም ሰው ተስማማም አልተስማማም፥ እኛ ግን በአንድ ሀቅ ላይ በዕርግጠኝነት ለመናገር እንፈልጋለን። ይኸውም፥ ለአለፉት ሠላሳ ዓመታት የኢትዮጵያን የፖሊቲካ ሥልጣን በመያዝ የተፈራረቁ ግለሰቦች፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ፥ የሚንቁ፥የሚጠሉ፥ የሚፈሩ፥ የሚያዋርዱ፥ የማያምኑ፥ የሚዘርፉ፥ የሚጨቁኑና የሚከዱ፥ በመጨረሻም ለአደጋ አጋልጠው የሚሸሹ መሆናቸውን ነው። ይህ ድምዳሚያችን ደግሞ፥ ማስረጃ አምጡ- ድገሙ የሚባልበት አይደለም። ምክንያቱም፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሳለፈው ተመክሮና መራራ ታሪክ ስለሆነ ነው። ምንም እንኳ የኢትዮጵያ ተፈራራቂ ገዥዎች ይህ ነው የማይባል ግፍና በደል ቢፈጽሙበትና በመጨረሻም በሕዝቡ ትግል ሊያልፉ ሊጠፉ ቢችሉም፥ እነርሱን የሚተካው፥ ካለፉት ጥፋት ተምሮ የሕዝብ አገልጋይ ለመሆን አለመጣሩ ነው። በመንግሥትና በሕዝብ መካከል ሊኖር የሚገባው ግንኙነት በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እስካልተመሠረተ ድረስ ደግሞ፥ ይህ መሆኑ የሚያስገርም አይሆንም።

በሃያ አንደኛው ምዕተ ዓመት ዋዜማ ኢትዮጵያን የሚገዙ ሰዎች፥ በ18ተኛውና በ19ነኛው ክፍለ ዘመን በነበሩት ፊውዳሎች ሥነአዕምሮ ውስጥ መኖራቸው፥ የሚያሳዝን ብቻ ሳይሆን፥ የሚያስገርምም ክስተት ሆኗል። ሕዝብን እያጭበረበሩ፥ እያታለሉ፥ እየፈሩ፥ እየተጠራጠሩ፥ እየዘረፉና እየጨቆኑ መግዛት ምን ያህል ኋላ ቀርነት ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም። በዘመነ ቴዎድሮስ የቀረውን የኅጥና የክልል ሥርዓት ማስፈንን፥ መለስ ዜናዊና ግብረ አበሮቹ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚል ቅብዐ ሜሮን ሰጥተውታል። ሁልጊዜ መልከ ጥፉን በስም ይክሱ መሆኑ የተለመደ ነው።

አምባገነኖች፥ ሕዝቡ ለአመፅ በሚዘጋጅበት ጊዜ አስቀድመዉ የመከላከያ ዘዴ በማሰናዳት፥ ከሚጠቀሙበት ዘዴ ለአጥፊ ጦርነት ማዘጋጀት ስለሆነ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወያኔ የጦርነት መያዣ ወጥመድ እንዳይገባ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት። የሀገርና የወያኔን ፍላጎቶች ተፃራሪነት ለአንድ አፍታም መዘንጋት የለበትም። ና ለሀገርህ ሞት ባዮቹ ሀገርን ገዳዮቹ ራሳቸው ናቸውና ሀገሬን መዳን ብሎ ሲነሳ ለጨቋኞቹም ዕድሜ እንዳይሰጥ መጠንቀቅ አለበት። በአሁኑ ወቅት ይህን ጥንቃቄ ማድረግ ያለበት በመለስም በኢሳያስም አገዛዝ ስር ያለው ሕዝብ ሁሉ ነው። ከአምስት ዓመት በፊት የተደረገው ጦርነት ከመቶ ሺ ሕዝብ በላይ አጥፍቶ የተገኘው ውጤት ባድመንና ዛላ አንበሳን ከነነዋሪዎቹ አሳልፎ መስጠት እንደሆነ፥ ገና ያልሻረ ቁስላችን ነው። ከዚያ ጦርነት ማን ተጠቀም ማን ተጎዳ ብንል በቅድሚያ ያለቀውና የተጎዳው ሕዝቡ ነው። አገዛዞቹ ኪሳራ ቢደርስባቸውም ከሥልጣን ሳይወገዱ ቀጥለዋል። ለወያኔ መሰሪ ቅስቀሳ አጉል ድምፅ የነበሩት ከሀዲዎች ደግሞ ያው ጥቅማ ጥቅማቸውን አግኝተው ረክተዋል። የሀገር መሬት አልተመለሰም-- ይሂድ ተብሎ ተፈረደበት እንጂ። ከባድሜ መልስ ወደ መለስ ሲባል የነበረውም ባዶ ልፈፋ ሆኖ ቀርቷል። አሰብን ያሰቡ በሀሳብና በምኞት ቀርተዋል። ከመለስ አገዛዝ ለውጥ የጠበቁ ጥበቃው ዘለዓለማዊ ሆኖባቸዋል። የእነ መለስ ስብስብ ሀገርን ሊያስከብር ሳይሆን፥ ሊያጠፉ የቆመ መሆኑ በማያወላዳ መንገድ ግልፅ ሆኗል። ዛሬም ሆነ ነገ ይህ ቡድን ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ሆነ ክብር የሚሰራው ቁም ነገር የለውም። ይህንን መገንዘብ ከቻልን ጦርነት ሲል የራሳችንን አስፈላጊ እርምጃ በመውሰድና አስፈላጊውን መስዋዕትነት ለራሳችን መብትና ለሀገራችን ሀቀኛ ሉዓላዊነት በመክፈል በቅድሚያ የመለስን ቡድን ከሥልጣን ማስወገዱ ላይ ማተኮር አለብን ማለት ነው። እባብን በጉያ ይዞ አውሬ አደን አይሰማሩም ነው። አልፎም በሕዝቦች መሀል የደም መፋሰስን መቃወም ተገቢ መሆኑን መዘንጋት አያሻም። በአጭሩ ኢትዮጵያን ለማስከበር የመለስ ዜናዊ ቡድን ላይ መነሳትና ማመፅ ከሁሉም በፊትና በላይ ግዳጃችን መሆኑን መርሳት የለብንም።